ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም

# ጎበዝ! አረጋዊ በርሔ ምን አሉ.... ?
# ድመት መልኩሳ፣ ዓመሏን አትረሳ!

ከአያልነሽ

እንዲህ ዓይነት ችግርግር ያለና በምድርም ሆነ በሰማይ መድኃኒት የማይገኝለትና የማይገኝላቸው በሽተኞች ሲኖሩብን፣ ጦሳቸው ከባድ መሆኑ ይታሰበንና የቸገረ ነገር ሆኖብን ሁሌም መቸጋገራችን አይቀሬ ይሆናል ። የሚያሳዝነው ደግሞ እንደነኝህ ዓይነት በሽተኞች አደገኛነታቸው *"__ሙት ይዞ ይሞታል__"* እንደሚባለው በመሆኑ በሽታው ይዞ እስኪደፋቸውና እስኪያጠፋቸው ድረስ፣ ጦሳቸው ከራሳቸው አልፎ እንወክልኃለን ለሚሉት ህዝብም አደጋን መጋረጡ ማየት አለመቻላቸው ነው። የበሽታቸው አስከፊነትና ክፋቱ ይሄ ነው። ለዚህ ነው ሙት ይዞ ይሞታል ያልኩት። የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር/ወያኔ (T.P.L.F) ውስጥ ተሠግስገው የቆዩና ያሉ የግንባሩ ሾፌሮችና መኃንዲሶች በሙሉ፣ ይህ ሠይጣናዊና አገርን አውዳሚ ተልዕኳቸውና ማንነታቸው በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ሲታወቅና ሲጋለጥ ደግሞ፣ በልብስ የሸፈኑት አውሬነታቸው በአደባባይ ወጥቶ አሳጥቷቸዋል። 40 ዓመት ሙሉ ከላይ ልብስ ለብሰው ሲታዩ ሰው እየመሰሉ፣ ውስጣቸው ግን በሸርና በሴራ የተተበተቡት እነዚህ ሰዎች፣ ይህ የሴራ አስተሳሰባቸው እርስ በርሳቸው ሲያጋድላቸው ኖሮ፣ ዛሬም እንዲተዳደኑ ከማድረግ አልተቆጠበም። ሴራና ሸር ልብሳቸው የሆነው እነዚህ የወያኔ ጉዶች ይህ በሽታቸው ትግራይን አደጋ ላይ ከቶ፣ ኢትዮጵያን ደግሞ እየተፈታተነ ይገኛል። ህወሓት/ወያኔ በትግራይ ተመሠረትኩ ካለ ጀምሮ ለ36 ዓመት እያንከባለለ ያመጣው ጣጣ እንወክልኃለን ላሉት የትግራይ ሕዝብ ተርፎ ህይወቱንም አስገብሮት እያለ፣ የትግራይ ህዝብ ዛሬ የተጋረጠበትን አደጋ ስናጤን በእጅጉ ያስቆዝመናል። እንደነርሱ (እንደመሪዎቻቸው) የሚያስፎክረን፣ የሚያስሸልለን ሳይሆን ይልቁንም ትግራይ በገዛ ልጆቿና ባሳደገቻቸው ክፋዮቿ የገባችበትና የተጋረተባት ፈተናና ጭንቅ 'እህህ!' አሰኝቶ አንገት የሚያሰደፋ እንጅ፣ የሚይስደነፋ ሊሆን ባልትገባ ነበር። በእነዚህ ሰዎች ጦስ፣ በዚህ መንደርተኛና ጎጠኛ ድርጀት ሳቢያ፣ የትግራይ ሕዝብ ከላይም ከወገኑ፣ ከታችም አካሉ ከሆነው ጋር ደም አቃብተው፣ የሾከ አጥር አበጅተውለት ከወገኖቹ ጋር ለማለያየት ብዙ ብዙ ጥረዋል። ከሁሉም በላይ አስጨናቂው ደግሞ ይህች የታሪካችን አካልና እምብርት ሆና የቆየችውና ያለችው ትግራይ፣ እዚያው በተፈጠሩ፣ እትብታቸውን ትግራይ መሬት በቀበሩ ልጆቿ አማካኝነት ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍና የሚወራረስ የታሪክ ጠባሳን ማሸከማቸው ነው። ትግራይ በታሪኳ እንደ ህዝብ ታሪኳን፥ ክብሯን፣ ኢትዮጵያዊነቷንና ኢትዮጵያዊ ገድሏን ያዋረዱ፣ የናቁና በኢትዮጵያዊ ታሪክ ዙሪያ በተጫውተችው ሚና ያፈሩባት በሙሉ፣ ከራሷ ከትግራይ መሬት የተወለዱና የወጡ የገዛ ልጆቿ መሆናቸው ደግሞ የምፀት ምፀት ነው። ታዲያ ለዚህ ጉድፍ ተጠያቂው እንዴት የአማራው ህዝብ ሊሆን ይችላል አቶ አረጋዊ....?

አቶ አርጋዊ በርሄና በዚያ ድርጅት ውስጥ የቆዩ፣ አሁንም ያሉ መሪ ነን ባይ ግለሰቦች በሙሉ ድርጅታቸው ህወሓትን ህወሓት ብለን የሰየምነው ወይም ስም የሠጠነው፣ ከቀድሞ አባቶቻችን በወረስነው ታሪካዊ ገደል ነው ይሉና የ1935 -36ዓ/ም በትግራይ ውስጥ የተደረገ አመፅን እንደማጠየቂያ ያቀርባሉ። የ1935/36 ዓ/ምቱ በትግራይ ውስጥ ተደረገ የሚሉት "**አመፅ**" ራሱ አጠያያቂ ቢሆንም፣ ያ በዚያን ወቅት የነበረውን የ"አባቶቻችሁን" አመፅና ተጋድሎ አክብራችሁ ስሙን ከወረሳችሁ፣ ምነዋ ዛሬ ይሄንን ስም ትታችሁ *"__ኢሕአዴግ__"* በሉን በማለት ትወተውቱናላችሁ...? ምነዋ ከወያኔ/ህወሓት በላይ ዛሬ "ኢሕዴግ" መባልን መረጣችሁ? ***ኢሕዴግ*** መባልስ አኮራችሁ...? እያልን መጠየቅ በቻልን ነበር። የሆኖ ሆኖ ግን የምንጠይቃቸው ሰዎች ጤነኝነት አጠያያቂ መሆኑ አልቀረምና እውነተኛ ወይም ጤነኛ መልስ ከእነርሱ መጠበቅ፣ ከዕባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል ብሎ እንደሚጠብቁ የዋሆች ሲያስቆጥረን ኖሯል። ይህ ብቻ

አይደለም። ያ (1935-36 ዓ.ም) ታሪክ ወይም አመፅ ለምን ለትግራይ ልጆች ብቻና በትግራይ ውስጥ ብቻ ታሪኩ እንዲነፀባረቅ ተፈለገ ....? ጥሩ ታሪክ ከሆነ እንዴት በአንድ "ክልል" ብቻ ተዳፍኖ ይቀራል...? እንዴት ይህንን ታሪክ ህወሓት/ወያኔ ብቻ እንዲወርሰው ተደረገ፣ ከቶ ለምን ይሆን....? እያልንም መጠየቅ ባልገደደ ነበር። ግን ምን ይሆናል ከዕብዶች መኃል አንድ ጤነኛ ካለ እርሱም እንደ ዕብድ ይቆጠራል ነውና ለአበዱት ምሕረት ያውርድላቸው ከማለት ሌላ ምንም ማለት አይቻልም።

እነ አቶ አረጋዊ በርሄ ለ40 ዓመት ሲያሴሩት የቆዩት ወያኔያው ተግባራቸው በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታወቅና ሲጋለጥ በእጅጉ ውስጣቸውን አሳፍሯቸዋል። በገሀዱ አደባባይ ግን ሁሉም የቡድኑ አጋፋሪዎች ኃፍረታችውን ሊቀበሉ አልደፈሩም፤ ይልቁንም ዛሬም ቢሆን ይህንን አገር አውዳሚነታቸውን የተለያየ ቅብ እየቀባቡ ሊሸፋፍኑት ይሞክራሉ። ለዚህም ነው ከዛሬ 30 ዓመት በፊት የተለዩት እናት ድርጅታቸው ስለሆነው ወያኔ/T.P.L.F አቶ አረጋዊ ሲናገሩ *"__እኔ ስጀምረው አጀማመሩ ደግ ነበር__"* በማለት ይህንን ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ቡድናቸውን ሊያሞካሹትና ሊያስማምሩት የሚዳዳቸው። አቶ አረጋዊ ሆኑ ሌሎች ባልደረቦቻቸው እስከአሁን ያልገባቸውና ሊቀበሉት የሚቸገሩበት ሃቅ፣ ወያኔና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተዋወቀው ሆድና ጀርባ መሆናቸውንና ይህንን ደርጅትና መሰል የመንደርና የጎጥ ጎረምሶች አስተሳሰብ (አስተሳሰቡን እንዳለ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ዶግ አመድ ማድረጉ ነው። ህዝባችን ህወሓት/ወያኔን ዓይንህን ለዓፈር ብሎ ምሎ መገዘቱ፣ ለእነ አረጋዊ በርሄ ሆነ ለነስዬ የመብረቅ ያህል ቢያስደንግጣቸውም፣ ማፈር የሚባል ነገር አልተፈጠረባቸውምና በእውር ድንብራቸው ሲወራጩ ይታያሉ። ቀፎና ባዶነታቸው ግልጥልጥ ብሎ ታይቷልና ሊሸፋፍኑ የሚጠቀሙበት ደግሞ ውድ ውድ የሆኑ ልብሶችን በመልበስ አትሮንስ ላይ ቆመው በባዶ እብሪት መደስኮሩን መርጠዋል። ይሄንን የእነርሱን ዲስኩር ደግሞ ለምደነዋል። የሚገርመው ከልጅነታቸው ጀምሮ በዚህ በጣም ኋላቀረ በሆነ አስተሳሰባቸው ሳቢያ በውስጣቸውም ቢሆን አክሱም፣ ሽሬ፣ አድዋ፣ አጋሜ፣ ተምቤን ወዘተ... በሚል የሥልጣን ሽኩቻ እየተጋደሉ እዚህ የደረሱ ለመሆናቸው ዛሬም የምናዬው ቀድሞም ሲተራመሱበት የነበረ ኃብታቸው ነው። እነ ስዬ ገብሩ አስራት ...ወዘተ በሙሉ የኃውዜን፣ የአደባባይ እየሱስ፣ የአርባ ጉጉ፣ የወተር፣ የአኙዋክ ወዘተ... ህዝብ ጅምላ ጭፍጨፋና ግድያ ደም የተጨማለቁ ሰዎች፣ ዛሬ ደርሰው '*__ጅብ ከማያውቁት አገር ...__*' *ነበር የሚባለው፣* በሚያውቃቸው ህዝብ መኃል የ*__"ሠላም ትግል፣ የዓረና ትገል፣ የመድርክ ትገል፣ የታንድ ትግል"__* መሪዎች ነን ብለው በድፍረት በአደባባይ ሲቀርቡ መመልከት፣ እነርሱ ባያፍሩ እኛ ግን ለእነርሱ በኃፍረት ተሸማቀን የምንገባበት አናጣለን። አቶ አረጋዊ በርሄም በእንዲህ ዓይነት ኋላቀር አስተሳሰባቸው ተሸፍነው፣ የድርጅታቸው ህወኃት/ወያኔ ሊቀ መንበርና የአጠቃላይ የድርጅቱ ወታደራዊ መሪ ሆነው በቆዩበት ሁኔታ፣ በውስጣዊ ድርጅታቸው ያለን ችግር በሙሉ የፈቱበት ፍቱን መድኃኒት፣ እየገደሉና እያጠፉ የመጡበተን ሂደት በቪ.ኦ.ኤ ላይ ሳያፍሩ *"__እያሸነፉ__"* እንደመጡ ደንፍተዋል። ይህንን ወደኋላ ላይ በሰፊው ለማሳየት እሞክራለሁ።

እንዲህ አሉ አቶ አረጋዊ በርሄ *"__T.P.L.Fን ስጀምረው/ስንጀምረው ጥሩ ነበር - የተበላሸውና መሥመሩን የሳተው በኋላ እንጅ__ "* በሚል የለመዱትንና የኖሩበትን በሬ ወለደ ቅዠትና የሕልም ሩጫቸውን ዛሬም አወድሰዋል። ይህንን ተረታቸውን ለራሳቸው ብቻ ደጋገመው ቢሰሙት ባልቸገረን ነበር- ነገር ግን ይህን እጅ እጅ የሚልና የሚያቅለሸልሽ ቅዥት፣ ዛሬም በጥብጠው ሊግቱን መነሳታቸው፣ እውነትም እንደሚባለው እነኝህ ሰዎች በሙሉ ነውርና ይሉኝታ የሚባል ነገር በመዘገበ ቃላቸው እንደሌለ አመላካች ነው። አረጋዊ በርሄ መኖሪያቸው አመስተርዳም/ሆላንድ ሆኖ *"ዶክተርም"* ሆኛለሁ ብለው እየነገሩን ባሉበት ሁኔታ፣ ***እድሜ ልኩን ውኋ ውስጥ የኖረ ደንጋይ ዋና አይዋኝም፣*** ይባላልና ዛሬም ከዛሬ 40 ዓመት በፊት እቆሙበት ላይ

EthioLion.com

ቆመው አለመነቃነቃቸውና ኢንች እንኳ አለመራመዳቸውን ጉድ የሚያሰኝ ነው። ታዲያ ይህ በሽታ ዕርግማን ካልሆነ በቀር ምን ሊባል ይችላል ወገኖቼ! ላዒላ ኢላላህ! ።

ሰሞኑን አቶ አረጋዊ በርሄ ከቪኦኤ ጋር ያደረጉትን ጭውውት በጥሞና አዳምጫለሁ። ወደ ቁም ነገሩ ከማለፌ በፊት በቅዳሚያ V.O.A. አማርኛው ክፍል ዝግጅትና የወቅቱን "ለጥያቄዎ መልስ" ፕሮግራም አዘጋጅና አቅራቢን ሳላመሠግን አላልፍም። አስከተዬም ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው አቶ አረጋዊ በርሄ ሊመልሱ ይገባቸዋል ያሏቸውን ጥያቄዎች በሙሉ መጥነውና ፍሬ ነገሩንም እያሰጨበጡ በማቅረብ ላፋጠጧቸው ጠያቂዎች በሙሉ፣ አክብሮቴ ከፍ ያለ ነው። ሁሉም ጠያቂዎች የጠየቁት ጥያቄ በሙሉ የሚወደቅ ነገር አልነበረውምና ኮርቸባችኋለሁ-ብራቮ!። ተጋባዡ እንግዳ ግን የተጠየቁ ጥያቄዎችን በመመለስ ፋንታ ምንም የማይገናኝ ነገር በማምጣት የባጥ የቆጡን ቀባጥረው *"የግራ፣ የቀኝ፣ የኋላ፣ የፊት"* ኃሳብ፣ አይዶሎጂ አላግቶኝ በማለት ጥያቄውን ሳይመልሱ ፈተናውን ወድቀው ተሠናብተዋል፡፡ ይልቁንም ለሚጠየቁት ጥያቄ ግልፅና ቀጥተኛ መልስ ከመመለስ፣ ካልቻሉም (አለመመለሰም እኮ ይቻላልና) አራባና ቆቦ በመርገጥ ማንነታቸውን አጋልጥው ***የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች*** ዓይነት ጨዋታ ተጫውተው ተለያዩ።

የወያኔ/ህወሓት መሪዎች በሙሉ ተመሳሳይ ታሪክ አላቸው። ዋናው የሚታወቁበት፣ ታሪክን አዛብቶ የማቅረብ ባህሪያቸው ነው። ይሄ ደግሞ አምላክ የተመሠገነ ይሁን ዕድሜ ሰጥቶን ከእኛም በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ በዓይኑ እየተመለከተው፣ በጆሮው እየሰማው፣ በህይወቱም እየከፈለበት ያለ እዳ መሆኑ እውነት ነው። እነአረጋዊ በርሄ የተሳሳተና የተዛባ የሐሰት ታሪክ ፈጥረው፣ ተራራ ያቀንቀተቀጠ ውሸትን ለብሰውና አጥልቀው፣ የባእድ እጅና ክንድ ሆነው በእነአረጋዊ በርሄ ዘመን (ጭምር) የተጀመረው (ለሱዳን፣ ለሊቢያ ወዘተ....) አሽከርነት ቀጥሎ፤ ድርጅታቸው ዛሬ መላ አገራችንን ለባዕዳን እየሸጠ ይገኛል። በተሳሳተ የኤርትራንም ሆነ የትግራይን ታሪክ ድሪቶ ደርተውለትና የሌለ ታሪክ ፈጥረው በቅድሚያ በትግራይ ውስጥ የትግራይ አዕሩጎች አዛውንት፣ ታሪክ ነጋሪዎችንና መካሪዎችን፣ ቀጥሎም የትግራይ ወጣቶችን ፈጅተው ሲያስፈጁ በጊዜው ዋናው መሐንዲስና ሾፌር፣ አቶ አረጋዊ በርሄ ነበሩ። በኋላም ከኢሕአፓ ጋር ደም ያቃባ ጦርነት የተገባበት ታሪክ፣ አረጋዊ በረሄ በቪኦኤ ላይ እንደቀደዱት ነጭ ውሸት ሳይሆን፣ አሁን ድርጅታቸው ህወሓት/ወያኔ በአቶ መለስና ስብሓት ነጋ የሚያከናውነውኑትን አገር አጥፊ ተልዕኮ በእንጭጩ በመቃወመችንና የትግራይ ህዝብም ከኢህአፓ ጋር ቆሞ ይታገላቸው ስለነበር ነው። ለዚህም ነው ከትግራይ ውጡልን ብለው ጦርነት ሲከፍቱ *"<u>አባይ ኢትዮጵያ</u>"* የሚለውን ስም የሰጡን እነአረጋዊ በርሄ ናቸው። *"<u>አባይ ኢትዮጵያ</u>"* ማለት ታላቂቱ ኢትዮጵያ ለማለት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በወቅቱ ከትግራይ ውጡልን ብለው እነአረጋዊ በርሄ ሲያስቸግሩንና ጦርነት ሲከፍቱብን መለሰ ዜናዊ በበታው አልነበረምና ነጭ ውሸት ነው አቶ አረጋዊ የዋሹት። በነገራችን ላይ ኢሕአፓና ወያኔ እንደ ድርጀት የተገናኙት በትግራይ ውስጥ ነው። አቶ አረጋዊ በርሄ ይህንንም ለመካድ ትዝታ በላቸው ወያኔ ከኢሕአፓ ጋር ለምን እንደታጋጨ ስትጠይቃቸው ምንም የማይገናኝና ያለነበረ ታሪክ አምጥተው የመለሱት መልስ ኢሕአፓ የከተማ አመፅ ሲል እኛ ደግሞ ከእነርሱ ቀደመን አይሆንም በትጥቅ ትግል በማለታችን ነው ማለታቸው በሳቅ ገድሎኛል ሐሰት። - ከመይ! ከመይ አሉ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ!

በዚያን ወቅት አሁን ለገሠ ዜናዊ ይዞት ያለውን ሥልጣን የሚመጣጠን ይዘው የነበረውና ጦሩን የሚያዙት አረጋዊ በርሄ ነበሩ። ከኢዲዩም ጋር የተጋጩት በእነአረጋዊ በርሄ ጠብ አጫሪነት መንሥዔ ነው። እውነተኛው ታሪክ ይሄ ነው- እኛም አለን፣ሌሎችም አሉ ሞተን አላለቅንምና ያዝ ያድርጉ አቶ አረጋዊ ማለት ያንስ ይሆን።

EthioLion.com

እስቲ አቶ አረጋዊ በርሄና መሠረትኩት የሚሉት ድርጀት ህወሓት/ወያኔ የቆመበትን የመሠረት ድንጋይ ለመመልከት እንዲያስችል አቶ አረጋዊ ሊነኩት ያልደፈሩትን የአደባባይ እውነት አብረን እንዳስሰው።
ሰሞኑን በV.O.A. አማርኛው ክፍል ***"በጥያቄዎ መልስ"*** ፕሮግራም ላይ የቀረቡት አቶ አረጋዊ በርሄና የድርጅታቸው ህወሓት/ወያኔ ውስጣዊ ይዘት፣ የተገነባውና መሠረቱ የተጣለው በአቶ አረጋዊ በረሄ መኃንዲስነት ነው። ይሄ እውነት ነው። ታዲያ ለአቶ አረጋዊ በርሄ በቪኦኤ ላይ ያልተነሱና በተለይ ደግሞ አረጋዊ በረሄን የሚመለከቱ ጉዳዮችን እያነሳሁ ለማሳየት ልሞክር።

ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ወያኔ የተቋቋመው አቶ አረጋዊ በርሄን ጨምሮ 7 ወይም 11 ግለሰቦች (ቁጥሩን ለእነርሱ እተውዋለሁ) - ለእንዲህ ዓይነት አገር ለሚያጠፋ ክፋት 1 ሰውም ቢሆን ከበቂ በላይ ነውና - ያቋቋሙት መሆኑ ይነገራል። ድርጅቱ የተቋቋመበት መሠረታዊ ጭብጥ ዛሬ ሁሉም የወያኔ መሥራቾች ሆኑ ቀጣዮቹ እነለገሠ ዜናዊ ሳይቀሩ የሚናገሩት፣ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለየ ጭቆናና የባህል ተፅእኖ ኖሮበት ሳይሆን፣ እውነቱ ከዚህ ፍጹም የተለየና በተግባርም ሠርተው እያሳዩት ያለ ሂደት በመሆኑ መረጃ ማጣቀስ አያስፈልግም። አቶ አረጋዊ በረሄ ከ1967 - 1974/5 ዓ.ም (ኢ.ት.አቆጣ)ድረስ የድርጅቱ ሊቀ መንበርና ብቸኛ የድርጅቱ ወታደራዊ መሪ በነበሩበት ወቅት፣ ያከናወኑትን መራራ እውነቶች ላስቀምጥ። አቶ አረጋዊ በርሄ ብዙ ጊዜ ሊያነሱ የማይፈልጉት ሃቅ ቢሆንም የእሳቸውን እውቅናና ይሁንታ እያገኘ የተከናወነው ድርጊት ነውና በጥያቄ መልክ ላቅረብ።

- የቅሌት አባት የሆነው ስብኃት ነጋ የተናገረውና የሚናገረው እውነት፣ እውነት ነውና፤ ለሻዕቢያ ሕልውና በሚል በሳኅል በረሃ ተልከው ሰላለቁት የትግራይ ወጣቶች ተጠያቂው ማን ነው? ያኔ አቶ አረጋዊ በርሄ በወቅቱ እርስዎ ነበሩ የድርጅቱ ዋና ሊቀ መንበርና ምን ይላሉ..?

- እርስዎ የድርጅቱ ሊ/መንበርና የድርጀቱ ወታደራዊ ተጠሪ በነበሩበት ወቅት መሠለኝ፣ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ለገበያ ልውውጥ ወደ ትግራይ ሲመጣና ትግራይ መሬትን ሲረግጥ የእርስዎ ወታደሮች ነበሩ በር በሩን ዘግተው በመጠበቅ የኮቴ ካልከፈልክ አትግባም እያሉት ለኮቴ ሲከፍል የኖረው። ይሄ ውሸት ነው...? በማን ማዘዣ? - አቶ አረጋዊ በርሄ ባወጡት ማዘዣ አይደለምን...? እና ታዲያ በቪኦኤ ቆይታዎ ላይ የወልቃየት ጠገዴ መሬትን ሕዝብ ሳይመክርበት አቶ መለስ ማካለሉ ልክ አይደለም ብለው ማለትዎ እርስዎ የጀመሩትና ያቀዱትን (በወቅቱ የትግራይ ሪፑብሊክ/ክልል በሚል ባስቀመጡት ካርታ መሠረት) ተግባራዊ አደረገ እንጂ ምን የተለየ ነገር ሠራ መለስ...? እረ ይብቃ! ዛሬም እኮ ያን የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ እየተዛባበቱበት ነው አያውቅም በሚል፡፡ አቶ አረጋዊ በርሄ እረ እየተስተዋለ! ***"አፍን ይበሉበታል እንጅ ከፉ አይናገሩበትም!***

- አቶ አረጋዊ በርሄ እስቲ በ1968 ዓ.ም (ኢ.ት.አቆጣ) "እንደራደር" ብላችሁ ትጥቅ ከአስፈታችሁ በኋላ አገር ሠላም ነው ብለው በተኙበት ስለተረሸኑት ስለተጋድሎ ሓርነት ትግራይ (TLF) አገዳደል ያጫውቱን.....? በማን ትዕዛዝ ? ለምን...? በወቅቱ የድርጅቱ ሊ/መንበርና የድርጅቱ ወታደራዊ መሪ የነበሩት እርስዎ ነበሩ አይደል....? እነርሱስ ኢሕአፓዎች ሆነው ይሆን? ወይስ አማራዎች?

- አቶ አረጋዊ በርሄ አሁን ለኢትዮጵያ ተቆርቁረው ስለ ባህር በር አስፈላጊነት ከተናገሩ እርስዎ የድርጅቱ የህወሓት/ወያኔ ሊ/መንበር በነበሩበት ወቅት

EthioLion.Com

*"የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው"* ብለው እርስዎ ላመኑበት ዓላማ ለኤርትራ "ነፃነት" ተሰልፈው የሞቱ የትግራይ ልጆች ቁጥራቸው ምን ያህል...ነው? አሁን መለስ ተግባር ላይ ያዋለውና የሚያውለው ዋና ዋና የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ ተግባሮች በሙሉ ያኔ የተፈራረማችሁት አይደለምን...? ይሄን ሁሉ ጉዳይ እስከዛሬ ለመናገርና የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ለመጠየቅ ለምን አልቻሉም...? ለምን አይደፍሩም...?

- በትግራይ ውስጥ እርስዎ ሊ/መንበር በነበሩበት ወቅት የተገደሉ የትግራይ አዛውንቶች፣ የወያኔን መስመር አንቀበልም በማለታቸው ለደርግ የተሳሳተ ዜና በማቀበል (ኢሕአፓዎች ናቸው) እያላችሁ በቀይ ሽብር ያስገደላችኋቸው የመቀሌ፣ የአዲግራት፣ የተምቤን፣ የአድዋ ...ወጣቶች ቁጥርስ ስንት ነው....?

- ስንት የትግራይ ወጣቶችን ወያኔን ካልደገፋችሁ ብላችሁ እምቢ ያሏችሁን ወደ ሱዳን፣ ሳውዲ አረቢያ፣...ወዘተ የተሠደዱና የተገደሉስ የሉም....? ይህንን እርስዎ አያውቁም እንዴ አቶ አረጋዊ....?

- ስለ አቶ ስዩ አብርሃ በመለስ መታሠር አግባብ አይደለም ካሉ.....ምነው የገዛ ሥጋ ዘመድዎ አቶ ሐጎስ አፅብሃ በ1981ዓ.ም (ኢት.አቆጣ) በእነሥዬ፣ ገብሩ አሥራት ከሱዳን ታፍኖ ከተውሰደ በኃላ በትግራይ ጉድጓድ ውስጥ ይሁን፣ የት እንዳደረሱት እስከዛሬ ስለማይታወቀውና ስለሚሰቃየው ሰው መናገር ፈሩ.....? ወዘተ

ውድ አንባቢዎች ሆይ!

ከህወሓት/ወያኔ መሥራቾችና ከድርጅቱ መሪዎች ውስጥ እስከአሁን ድረስ እውነቱን የተናገረው የቅሌት አባት የሆነው ስብሓት ነጋ ብቻ ነው። ስብኃት ነጋ የነገረንና አስምሮበት ያለፈው ሓቅ በሙሉ አሁን የወጡትም ሆኑ ያሉት የድርጅቱ መሪዎች በሙሉ የሚጋሩትና የሚስማሙበትን እውነት ነው የገለጠው፤ እነኝህ ሰዎች የራሳቸውን ሰዎች (የትግራይ ህዝብን) ሳይቀር ያስገደሉበት፣ የማገዱበትን ታሪክ ያጫወተን።...ወደፊትም ሊያደርጉት የሚያስቡትን ሕልማቸውን ነው የሚናገረው። እንዲህ አለ አቦይ ቅሌት! እናንተ ሰዎች *"ሕገ-መንግሥታችንን"* አናስነካም፤ ከነካችሁ ግን ጓዛችንን ጠቅልለን አሥመራንም አጠቃለን....ቀንዲ አፍሪካ (የአፍሪካ ቀንድ) አውራ እንሆናለን ብሎ ነው የነገረን። ይሄ ታሪክ አቶ አረጋዊ በርሄ በነበሩበትም ጊዜ አባሎቻቸውን ሲግቷቸው፣ ሲያጠጧቸው የነበረ ነው። ግን ያኔ ለአባሎቻቸው በዚህ መንገድ አልነበረም ሲነግሯቸው የነበረው። ምን ችግር አለው፤ ዴሞክራሲ ባልነበረው፣ በአንድ ሊቀ መንበርና ወታደራዊ መሪ ሁሉ ነገር በሚፈለጥ በሚቆረጥበት እንደ ወያኔ ዓይነት ድርጅት ውስጥ የሚጠይቅ፣ የሚናገር አባል፣ ይኖራል ወይም ይገኛል ብሎ ማሰብ የወያኔን ውልደት፣ እድገትና እንዲሁም ባህሪ የማያውቅ ብቻ መሆን አለበት። ስብኃት ነጋ የነገረን በሙሉ በቀላል አማርኛ ከዚህ በላይ ያስቀመጥኩትን ነው።

ሌላው ከህወሓት/ወያኔ ድርጅት አባል ውስጥ እውተኛውን ሐቅ የተናገሩት አቶ ገ/መድህን አርዓያ ናቸው። አቶ ገ/መድህን አርዓያ ለትግራይ ህዝብ ባላቸው አክብሮትና ለኢትዮጵያም ባላቸው ፍቅር ይህ ድርጅት ህወሓት/ወያኔ የሄደበትና የሚሄድበት መንገድ አደገኛ፤ በተለይ የትግራይን ሕዝብ ክብርና ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ውስጥ እየከተተ ያለ በመሆኑ ለትግራይ ህዝብ የማይበጅ፤ የትግራይንም ህዝብ ክብር የሚያጎደፍ ነው በማለት ድርጅቱን ጥለው ወጥተው ድርጅቱንም አምርረው ኮንነዋል፣ አውግዘዋል። በዚህ ድርጅት ውስጥ ሆኘ ባለማወቅ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማሳዘኔና የኢትዮጵያን ህዝብንም በመውጋቴ ተንበርክከኬ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ

እጠይቃለሁ፣ ጠይቄአለሁም ብለው፣ አሁንም ደጋግመው ከልባቸው (ይቅርታ) ጠይቀዋል። የትግራይ ህዝብም ከቀሪ ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ሆኖ ይህንን ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ቡድን ከሥልጣን እንዲያወረድ ተማጽነው በእነኝህ ፀረ ኢትዮጵያ ቡድኖች የጎደፈ ታሪኩን ያድስ ዘንድ፤ ለትግራይ ህዝብም ጥሪ አቅርበውለታል። እንዲህ ዓይነት አኩሪና ከእራሱ የህሊና ዳኛ ጋር የታረቀ ሰው ከወያኔዎች ውስጥ ማን አለ....? እከሌ ብሎ የሚጠቁመኝ ሰው ይገኝ ይሆን! እናም አቶ አረጋዊ ሆይ!"***<u>ዕብድ ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው</u>***" ተብሏልና ድርጅትዎን ህውሓት/ወያኔን 30 ዓመት ተለይተው ይኑሩ እንጅ አስተሳሰበዎና ህልምዎ ዛሬም ከጎጠኝነትና ከመንደርዎ አልዘለለም እልዎታለሁና እባክዎ ከእንቅልፍዎ ይንቁ! ***ድመት መልኩሳ አመሏን አትረሳ*** አሉ።

የሕዝብ ድምፅ ይክበር! የታሠሩ የፖለትካ እስረኞ በሙሉ ይፈቱ
ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን ዘመዶቼ
February 4/2010

EthioLion.Com